# አልተኛንም፣ አለን ለማለት?

**ዋለ አምባው** 01/20/14

ከቀጣዩ ብሄራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ ጽንፈኛው አክራሪ የዲያስፖራ ተቃዋሚ በሀገር ውስጥ ለሚንቀሳቀሱት አጋሮቹ በቅርቡ ቀጭን ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡ ምእራባውያንን በማግባባት በአውሮፓ ሕብረት፤ በአሜሪካ ሴኔተሮች፤ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትም እንዴት ተጽእኖ ሊያሳድሩና መንግሥትን "አጣብቂኝ" ውስጥ ሊከቱ እንደሚችሉ እየመከሩና ለራሳቸው መፍትሄ ያሉትንም እየቀመሩ ይገኛሉ፡፡

ይህንን በውጭ በበላይነት የሚመራው ግንቦት ሰባት ሲሆን፣ ሕዝቡን ለተቃውሞ የማነሳሳትና ጥላቻን የማዛማት ስራ በገሀድም በስውርም እየሰራ ይገኛል፡፡ ለዚህም የአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችንና ዓባላቱን በተለያየ ስምና ሽፋን ወደ አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለቅስቀሳ አስማርተዋል፣ሊያሰማሩም በዝግጅት ላይ ናቸው እየተባለም እየተነገረ ነው፡፡

ከዲያስፖራው አክራሪ ተቃዋሚ ምስጢራዊ በሆነ ሁኔታ የተላለፈውና ያፈተለከው አደገኛ ሴራ ዓላማው ሕዝቡን ለተቋውሞና ለአመጽ ለመቀስቀስ ያነጣጠረ ነው። በቅርቡም ተጨማሪ አዳዲስ ጋዜጦችና መጽሄቶች በአመዛኙ ከውጭ በሚደረግላቸው ከፍተኛ የገንዘብ ድጎማ በተለያዩ ግለሰቦች ስም ፈቃድ በማውጣት፤ አንዳንድ የቀድሞ "ጋዜጠኞችንና አምደኞችን" ከጀርባ በማሰለፍ የማነሳሳት ስራ እንዲሰራ ለማድረግም ይንቀሳቀሳሉ፡፡

በተለይ አንዳንድ የግል ሚዲያዎች ጋዜጠኞቻችን ተከሰሱ፣ታሰሩ፣ ቢሮአችን ተዘረፈ፤ ኮምፒዩተሮቻችን ተወሰዱ፤ጋዜጠኞች ጠፉ፤ ማንነታቸው ባልታወቁ የጸጥታ ሀይሎች ተወስደው የት እንዳሉ አይታወቅም፣እኛም ለሕይወታችን ስለምንሰጋ በነጻነት መስራት አልቻልንም፤ ወዘተ የሚሉ ሃሰተኛ ክሶችን በየጊዜው በማሰማት ድጋፍ ለማሰባሰብ ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸውና ይህንንም አሁንም ድረስ እያራመዱት ያለ አቋም እንደሆነ ይታወቃል።

ሌላው አስገራሚ ጉዳይ ደግሞ ሰሚ አላገኙም እንጂ ከአክራሪነት ጋር በተያያዘ በሕግ ቁጥጥር ሥር የዋሉ ተጠርጣሪዎችን ሽፋን በማድረግም ሃሰተኛ አሉባልታ በመንዛት

ሰላማዊ ሙስሊሙን ህብረተሰብ በተሳሳተ አቅጣጫ ለመምራት ሲማስኑ ተስተውለዋል። ሕዝበ ክርስትያኑንም እርስ በርሱ ለመከፋፈል ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም ማለት ይቻላል። ይህን አደገኛ ሥልታቸውንም በተለይም ከጸረ ሽብር አዋጁ ይሰረዝ ከሚለው አቋማቸው ጋር አያይዘው በቀጣይ ሊጠቀሙበት እንዳቀዱ አንዳንድ መረጃዎች ከወዲሁ እያመላከቱ ነው።

አክራሪው ዲያስፖራ ከፍተኛ ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ ማስገባት እንደማይቻል ስለሚያውቅ ተመራጭ አድርጎ የወሰደው የተለያዩ የንግድ  ዘርፎችን በመጠቀም ከትርፉ ከፍተኛ ገንዘብ በምስጢር ለጸረ ሰላም ኃይሎች እስከማስተላለፍ ሊደርስ የሚችል ስልት ሊከተል እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይህም በአገር ውስጥ ለማካሄድ ላሰበው ተቃውሞ ማቀጣጠያነት ለመጠቀም አቅዶ እየሰራ እንደሆነ እመላካች ነው።

ሕዝቡን ከፋኛ ምሬት ውስጥ ሊከተው ይችላል ባሉት መንገድ ሁሉ ለተቃውሞ እንዲነሳ በብዙ መልኩ የተጠነሰሰው ሴራ "መንግስት ለመምራት፣ ለመቆጣጠርም ሆነ ለማስተዳደር አልቻለም፣ አብቅቶታለታል፤" የሚል ተልካሻ አስተሳሰብ ሕዝቡ ውስጥ እንዲፈጠር ለማድረግ የተቀመረ ርባና ቢስ ስልት ነው። እዚህ ላይ ምናልባትም በቢሮክራሲው ውስጥ ያሉ አባላቶቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን በመጠቀም በመስተዳድርም ሆነ በአገልግሎት ሰጪ የመንግስት ተቋማት ባለጉዳይ እንዲጉላላና በመልካም አስተዳደር እጦት እንዲማረር በማድረግ፤  የህዝብ ተቃውሞ ለመጫር ጥረት ሊያደርጉና አንዳንድ ወገኖችን ሊያሳስቱ እንደሚችሉ መጠርጠርና ከወዲሁ ሁኔታዎችን በቅርበት መከታተል ተገቢ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

ለተደጋጋሚ ውድቀት የበቃውን የቀለም አብዮት፤ አለያም ካለፉት ሦስት ዓመታት ጀምሮ የተከሰተውን የአረቡን ዓለም ትርምስ ዓይነት በመጠቀም ሕዝባዊ መነሳሳትና አመጽ በማነሳሳት መንግስትን በኃይል በማስገደድ መለወጥ ይቻላል የሚል እምነት የያዘው ተቃዋሚው  ጽንፈኛ ሀይል ሌሎች ጸረ ሰላምና ኢ-ሕገመንግሥታዊ አማራጮችንም ከመሞከር ይታቀባል ብሎ ለማሰብ አይቻልም።

እነዚህ ሀይሎች ሁሉም ነገር ተገለባብጦም ቢሆን እነርሱን ወደ ስልጣን ያምጣቸው እንጂ ሕዝብ ቢተላለቅ፣ሰላም ቢጠፋና የፈለገው ዓይነት ልማት ቢስተጓጎል ቁብ የሚሰጣቸው አይደሉም። የእስላማዊው አክራሪ ሀይል በአገር ውስጥና በተለይም በአጉራባች የምስራቅ አፍሪካ አካባቢዎች የሥጋት ምንጭ በሆነበት ሁኔታ ላይ እንኳ ይህን አሳሳቢ ችግር

“የመንግሥት የፖለቲካ ጨዋታና የስልጣን ማራዘሚያ ዘዴ ነው” በማለት ሲሳለቁበት ይደመጣል፡፡

እንዲያውም በኢትዮጵያ አንዳችም የአክራሪነትና የሽርተኝነት ሥጋት የለም፤ የመንግሥት ትያትር ነው በማለት በይፋ የአክራሪዎችን እንቅስቃሴ ከመደገፍ ባልተለዬ መልኩ አቋማቸውን እያንጸባረቁ ይገኛሉ። የአልሸባብ አጥፍቶ ጠፊዎች በኢትዮጵያና ናይጀሪያ የእግር ኳስ ጨዋታ ታዳሚ ሕዝብ ላይ ወጥነውት የነበረው የፈንጂ አደጋ “ደባ ራሱን፣ስለት ድጉሱን” እንደሚለው የሃገራችን ብሂል በራሳቸው ላይ ፈንድቶ መክሸፉ በገሀድ እየታየና አልሸባብም ሃላፊነቱን ወስዶ ሳለ “ድርጊቱን ያቀነባበረው መንግስት ነው፣ ይህን ላለማድረጉም እርግጠኛ መሆን አይቻልም………” በማለት በወገንና በሃገር ደህንነት ላይ የተሳለቁ አንዳንድ በእብሪትና በማን አለብኝነት ስሜት ተወጥረው ሊፈነዱ የደረሱ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን የኢትዮጵያ ሕዝብ በእጅጉ ታዝቦአቸዋል፣አዝኖባቸዋልም፡፡

እነዚህ ሰዎች ማንን ደግፈው እየተከራከሩ ነው? የሚል ጥያቄም ያስነሳል። ምናልባትም እዚሁ አጠገባችን ባለችው የኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ውስጥ በቅርቡ በአንድ የገበያ ማዕከል ውስጥ አሸባሪዎች የፈጸሙት ጥቃት የተቀነባበረው በኢትዮጵያ አለያም የበለጠ ከደፈሩም ድንበር ተሻግረው በኬንያ መንግሥት ነበር ብለው በማስወራት “ሰርፕራይዝ”ሊያደርጉን አይዳዳቸው ይሆን? በዬ በግሌ አስባለሁ።

ጽንፈኛ ተቃዋሚዎች ዋናው ግባቸው ከየትኛውም በፕላኔታችን ላይ ካለ ጸረ ሰላም ኃይልም ጋር ቢሆን በመተባበር መንግሥትን በኃይል ከስልጣን ማውረድ፣ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን ማፈራረስ፣የሕዝቦችን መብት መጨፍለቅና የራሳቸውን ፍላጎት በኃይል በሕዝቡ ላይ መጫን ነው፡፡ ለሰላማዊና የበሰለ የፖለቲካ ውድድር አማራጭ ስፍራና ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኝነቱ በእጅጉ ይጎላቸዋል። ጭፍን ተቃውሞና ጥላቻ በሀገሪቷ፤ በሕዝቧ፤ በተጀመሩ ልማቶችዋም ላይ ምን ዓይነት አደጋ ሊያስከትል ይችላል? ብሎ ለመፈተሽና ለማመዛዘን ያልቻለ፤ በጥላቻና በስሜታዊነት ተሞልቶ የፈለገው ይምጣ በሚል እየሰገረ ያለ ተቃዋሚ ለሃገርና ለሕዝብ ጠብ የሚል አንዳች ውጤት ያስገኛል ብሎ ማሰብ ከእባብ እንቁላል እርግብ መጠበቅ ይሆናል።

በሰላማዊ የፖለቲካ ውድድር የተሻለ አማራጭ ፖሊሲ አለን ካሉ ይህን ለሕዝብ በማስረዳት ማሳመን፣ የደጋፊዎቻቸውን ድምጽና ይሁንታ ማግኘት እጅግ የተመረጠውና የሰለጠነው ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ አካሄድ ነው። እነዚህ ሁሉ የተሻሉ አማራጮች እያሉ የጥፋት

አቅጣጫ መያዝ ግን  ለሀገርና ለሕዝብ አይበጅም፡፡ ተቃዋሚው በመጀመሪያ ደረጃ በውስጡ ገኖ የሰፈነውን ድንበር የለሽ ጥላቻና ስሜታዊነት ማስወገድ፤ ለጋራ ሀገር ተቻችሎና ልዩነትን ጠብቆ መስራት ይቻላል ብሎ ራሱን ማሳመን ይኖርበታል፡፡

መንግሥት የራሱ ጠንካራና ደካማ ጎን አለው፡፡ ለኢትዮጵያ ይሄን ይሄን ታላቅ ስራ ሰርቷል፣ ይሄና ይሄ ደካማ ጎኑ ነው፤ መለወጥና መታረም ይገባዋል፤ ይሄን ለመለወጥ ደግሞ እኛ በዚህ-በዚህ አማራጭ ፖሊሲና ፕሮግራም እንሰራለን ማለት ትልቅነትም ጨዋነትም ነው፡፡ አሁን የሕዝብ ውክልና ይዞ ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ኢትዮጵያን ወደ ፈጣን ዕድገት እየወሰዱ ያሉና የሕዝብ ተጠቃሚነትን ያረጋገጡ ብሎም ቀጣዩ ትውልድ የሚኮራባቸውን ስኬቶች እያስመዘገበ ያለ ነው። ይህን ነባራዊ ሁኔታ ግን ለራስ ፖለቲካዊ ትርፍ ለመሸመት ሲባል ብቻ ማጣጣልና መካድ ትዝብት ላይ ይጥላል። ከዚህ ይልቅ እስካሁን በመንግሥት ለተከናወነውና እየተከናወነ ላለው መልካም ስኬት ተገቢውን ዕውቅና ሰጥቶ ከዚህ የላቀ ውጤት ለማምጣት ያስችላል የሚሉትን የራስን የተለየ ግልጽ ስትራቴጂና ፕሮግራም አውጥቶ ይህንኑ ለሕዝብ ማስተዋወቅ የበሰለ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ነው። ዞሮ ዞሮ ለሕዝብና ሃገር ጥቅም እንሰራለን እስካልን ድረስ በየትኛውም መንግሥት የተከናወነን መልካም ተግባርና የተገኘ ስኬትን ሁሉ የጋራችን አድርገን የመውሰድ ባህልን ማዳበር ይገባናል። ምንም ዓይነት የፖለቲካ አመለካከትና ዕምነት ልዩነት ቢኖር እንኳ በሃገራዊ ጥቅሞችና ደህንነት መረጋገጥ እንዲሁም በዋና ዋና ሃገራዊ አጀንዳዎች ላይ /በተወሰነ ደረጃ የስልት መለያየት ሊኖር እንደሚችል ታሳቢ ቢደረግም\ አንዳችም መሰረታዊ ልዩነት መፈጠር ግን አይኖርበትም።

መንግሥት ምንም አልሰራም፤ በኢትዮጵያ የታየ ለውጥ የለም፤ ጭራሽ ሀገሪቷን ገድሎአታል፤ ብሎ አፉን ሞልቶ የሚከራከር አክራሪና ጨለምተኛ ተቃዋሚን ለመስማት በእነሱም የጥላቻ ቅስቀሳ  ተገፋፍቶ ከተያያዘው ፈጣን የልማት እንቅስቃሴ የሚዘናጋ ዜጋ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡  እንደ አንድ ነጻ ዜጋ በግሌ እስከ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አገር ተረክቦ ለመምራት ይችላል ተብሎ ሙሉ እምነት የሚጣልበት ጠንካራና አማራጭ ተፎካካሪ የፖለቲካ ኃይል ለማየት የታደልን አይመስለኝም።

አበው "ከአነጋገር ይፈረዳል፣ከአያያዝ ይቀደዳል" እንዲሉ በርካታ የቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮችን  ሕዝቡ ተደጋጋሚ ኪሳራና ውድቀት ላይ እያገኛቸው ተከታዮቼ ናቸው የሚላቸው ብዙዎች ደጋፊዎቹ እንኳ ተስፋቸውን ሊጥሉባቸው አልቻሉም፣ዋጋ አስከፍለውታልና፡፡

እናም ሁሉም ባለድርሻዎች ሰክነው በትልቁ ማሰብና ማስተዋል፤ ከእልህ፣ ከጥላቻና ከቂም በቀል በመውጣት፤ በሰላምና በፍቅር ተከባብሮና ተባብሮ ለሀገርና ለሕዝብ መስራትን መርሃቸው ሊያደርጉ ይገባል። ይህ ሳይሆን ቀርቶና እንዲሁ “አለን” ለማለት ብቻ የጥፋት አቅጣጫን መከተል ግን  መዘዙ ብዙ ነውና  ሀገርንና ሕዝብንም ይጎዳል፡፡